ካሰላህ ጋር



ሰላታሚ
ኑጁሲ ጣተማያ ቤት

ሰዘጋጅ
ሙሐመድ ሰዒድ (ABX)

ከአላህ ጋር

በሙሐመድ ሰዒድ



ነጃሺ ማተሚያ ቤት

ማውጫ

መግቢያ 6
እመሰገንኩህ 7
መጽሐፍና ርዕስ 8
እፒታይዘር 11
ጹዓ ያስፈልገሻል 13
በሳሊሖች መካከል የተገኘሁ ሰታ 18
ማን እንዳገኘኋ 20
አምስት የብርታት መርፌዎች 26
ማስታወሻ 29
በዚህ ሰዓት መስጊድ ውስጥ ምን ትሠራለህ? 31
ኩሹዕ እና ሕይወት 35
ማስታወሻ 38
ወዳጄ ድቺን ሰዓት 40
ሰው እና ፈተና 44
ያ ረብ፣ እንሳሰን 48
ከቁርአን ጋር 50
በየእርከኑ አልተብየንም 55
እንዴን ያዝ 59
ማስታወሻ 62
በሃሳብ ራስን ስለመቻል 63
ምን ያሳስበናል? 68
ማስታወሻ 75
ከአላህ ጋር ሰድገት 76
ከአላህ ሥም 'አል-ዐፉው' ጋር 78
ማስታወሻ 81
ጊዜና ዓሳማ 83
ሕይወት አስተማሪችኛ 87
የልጅነት እርሾ 99

ማስታወሻ 103
የመንድም ዱዓ ዋጋ 105
ስራስ መድረስ 107
ማስታወሻ 108
ስለ ምርጥ የመጨረሻ ቃል 109
ማስታወሻ 110
ዱዓን የመግዛት ጥበብ 111
ደስም ይልሻል 114
ማስታወሻ 118
ከማን ጋር መሆን እንዳለባችሁና እንደሌለባችሁ 119
ሚዛናዊነት - በኛ እና በሌሎች መካከል 123
ማስታወሻ 125
ኸልዋ - ከአላህ ጋር የመሆን ድባብ 127
እንዲያ ነው ነገሩ 129
ልፋት እና ተስፋ 131
ማስታወሻ 134
ጀማዓው እንዲህ ሆኗል 135
ማስታወሻ 140
ብትወደኝማ ኖሮ 143
የማለዳ ትረፋት 146
በዚያው ዙርያ እንሽከርከር 147
ስንብት 150

መግቢያ

ነገሮችን ሊጀምሩት በሚግገባ ነገር እንጀምራለን -በአላህ ሥም እጅግ በጣም አዛኝ፣ እጅግ በጣም ርኅሩኅ በሆነው አምላክ እንጀምራለን። ምስጋና ለአላህ ይሁን። የአላህ እዝነትና ሰላም በአላህ መልዕክተኛ፣ በቤተሰቦቻቸው፣ በባልደረቦቻቸው እና በተከታዮቻቸው ላይ ሁሉ ይስፈን። ቢናገሩት፣ ቢናገሩት፣... ስለማያልቀው ጉዳይ ለመናገር ተመልሰን መጣን። ስለ ዲናችን፣ ስለ መንፈሳዊነት፣ ዛሬም ነገም አዋጭ ስለሆነው ጉዳይ ...

ይህ መጽሐፍ በዓለማቀፍ ደረጃ በተከሠተው በኮሮና ወረርሽን ምክንያት ወደቤቴ በገባሁበት የአራት ወር ጊዜ ውስጥ ነበር የተፃፈው። ይህ ጊዜ በመጠኑም ቢሆን ሥራ ላይ ውሏል ማለት ነው -አልሐምዱ ሊላህ። ጊዜያቱ በርግጥም ለኔ መልካም ዕድሎች ነበሩ። የጥሞናና የአስተውሎት ጊዜያት ነበሩ። ወደራሴ ለመመልከት ብዙ ጠቅመውኛል። በነኚህ ጊዜያት መስጊዶች ተዘግተዋል፤ ጁሙዓና ጀማዓ ቀርቷል። ደፅዋዎችን የመስማት ዕድሎችንም ተመናምኗል። ስለዚህ ራስን ለማስታወስና በኢማን ድባብ ለመኖር መላ መዘየድ ግድ ነበርና ነው በዚህ መጽሐፍ ውስጥ መቆየት የመረጥኩት።

በሕይወት ያለ ሰው የአላህ ፈቃዱ ከሆነ በምንም ይሁን በምን አጋጣሚና መስመር ይገናኛል። ዛሬ ደግሞ የመገናኛ መንገዱ በዝቷል። ይኸው የአላህ ፈቃድ ሆነና በዚህ መጽሐፍ በኩል ተገናኘን። አልሐምዱ ሊላህ!። የሞተ ሰው ግን በቃው።

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚያገኟቸው የተለያዩ መጣጥፎች ከአላህ ጋር በሚያስተሳስሩን በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ያተኮሩ ናቸው። ጊዜ ወስደው ቢያነቧቸው ይጠቅሟችኋል ብዬ አሰብኩኩ። መልዕክቶቹ ከሕይወት ልምድ የተገኙ፣ የረጅም ጊዜ ቁጭ ብሎ የመማርና የንባብ ውጤት የሆኑ ናቸው። ጽሑፍ ራስን የማስታወሻ እና የማጠንከርያ አንዱ መንገድ ነው። በዚህም ለራሴ ያልኩት ለናንተ ሆነ። አብረን እናንብብ።

ሙሐመድ ሰዒድ

መስከረም 2013

አመሰግንኩህ

ያ ረብ... ዛሬም በሕይወት ቆይቼ አንተን ለማመስገን በመታደሌ አንዴት ዕድለኛ ነኝ!። እንዳውቅህ ስላደረግከኝ በእጅጉ አመሰገንኩህ። አንተ አንተን እንዳውቅህ ባታደርገኝ ኖሮ ለምስጋናህ መቼ እታደልና!!። ለምስጋናህ መብቃት መታደል ነው። በፈቃድህ ወደ ራስህ ስለመራኸኝ ላመሰግንህ። ስላንተ እንድጽፍ ውስጤን ስላነሳሳህ፣ አዕምሮዬን ስላነቃህ፣ እጄን ስለመራህ፣ አንደበቴን ስላገራህ አመሰገንኩህ የኔ ጌታ። ስላንተ ለማውራትም ሆነ ለመግለጽ ቋንቋዬ ደካማ፣ ሥራዬ ልፍስፍስና ጥራት የሌለው ከመሆኑ ጋር በአንዳንዶች ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው በማድረግህ አመሰገንኩህ ረቢ ኪያ።

የወደቅኩ ሰው ከመሆኔ ጋር ሰው ሆኜ ለሌሎች እንድታይ ስላደረግከኝ፣ ከጉድለቴ ጋር ስለጠገንከኝ፣ ከከፍተቴ ጋር ስለሞላኸኝ አመሰገንኩህ አምላኬ። በራሴ ሁኔታ ባፍርም፤ በሥራዬ ብሸማቀቅኩም፣ በቅርብ የሚያውቁኝ ሰዎች እንዲህ እንዲህ እኮ ነው ብለው ቢያነውሩኝም... አንተ ግን በግልጋሎትህ ላይ አሰማርተህ ከብርን አጎናፀፍከኝ። ውስጤ ቆሸሸል ብዬ ስላንተ መፃፍ መናገር አልተውም የኔ ጌታ። ከወንጀል መቶበት ያቃተኝ ደካማ ባርያህ ነኝ። አንድ ቀን ሰው ታደርገኛለህ ብዬ ይኸው ያለአንዳች እፍረት በደጅህ አመላለሰሉ የኔ ጌታ።

ሁሌም በሁሉም ሁኔታዬ ውስጥ አመሰግንሃለሁ፤ ሁሉም የዓለም ቋንቋ ብችል ውዳሴዬ ላንተ ነው። ባዝንም ብደሰትም፣ ባጣም ባገኝም፣ ያንተው ነኝ። ካንተ ውጭ አምላክም ሆነ አለቃ የለኝ። ባርነቴ ላንተው ነው። ክጀላዬ ካንተው ነው። ስለ ብዙ ፀጋዎችህ አመሰገንኩህ፣ ስለ በርካታ ችሮታዎችህ አጎነበስኩልህ፤ ሰገድኩልህ። አምላኬ ሆይ! ካንተ ጋር ዕድሜ ልኩን ተጣብቆ መኖር እየተመኘ ያልሆነለትን ይህን ምስኪን ባርያህን እርዳው። የባሮችህን ውርደት የምትሰትር፣ ጉድለታቸውን የምትሸፍን አምላክ ሆይ! ሁሌም ሽፈናህ አይለየኝ። በጥበቃህ ውስጥ አኑረኝ።

መጽሐፍና ርዕስ

ወዳጆቼ... ለኔም ለናንተም ሊጠቅም ይችላል ብዬ ያሰብኩትን አንድ መልዕክት አስተላልፍ ዘንድ ፍቀዱልኝ...

የአንድ መጽሐፍ ርዕስ ከይዘቱ ጋር በእጅጉ መመሳሰል አለበት ብዬ አምናለሁ። ሰዎች ርዕሱን ብቻ አይተው ይዘቱን ለመረዳት ያስችላቸዋልና። ርዕስ ከመጽሐፉ ይዘት፣ የውስጥ ፍሰትና እንዲሁም ውበት ጋር መመጣጠን አለበት ብዬም አስባለሁ።

የአንድ መጽሐፍ ርዕስ መጽሐፉ የሌለውን ነገር ማንፀባረቅ የለበትም። ከመጽሐፉ ይዘትና የሃሳብ ከብደት በላይም መሆን የለበትም። ለማይረባና እውስጡም ባዶ ለሆነ መጽሐፍ ርዕሱን ማሳመርና ማጋነን ተገቢ አይደለም። አንባቢንም ሆነ ራስን ማታለል ነው የሚሆነው። ዩ ቱዩብ ላይ ርዕሱን አጋነውና ሳቢ አድርገው ጽፈው ውስጡን ባዶ እንደሚያደርጉት ማለት ነው። ወይም ላዩን ጥሩ ፍሬ ከምረው ውስጡን ገለባና ሹፉሮ እንደሚያደርጉት የኩንታል እህል፣ የማዳበርያ ከሰል ወይም ሌላ ነገር ማለት ነው። ...

እነኚህ ሁሉ "መን ገሸና ፈለይሰ ሚንና/ ያታለለን ከኛ አይደለም/" የሚለው ነቢያዊ ሐዲሥ ይመለከታቸዋል። ነቢያችን (ሰ.ዐ.ወ.) ይህንን ቃል የተናገሩት አንድ ከምር እህል ሻጬ ላዩን ደረቅ ውስጡን እርጥብ አድርጎ ለገበያ አቅርቦ ባዩ ጊዜ ነበር። ከሐዲሡም ባለፈ ሰው ለንፁህ አዕምሮው መኖር ይኖርበታል።

ስለሆነም አንድ ፀሐፊ ለአንድ መጽሐፍም ሆነ ሌላ ነገር ርዕስ የሚጨነቀውን ያህል ለይዘቱም መጨነቅ አለበት። ውስጡ ብዙም ያልተለፋበት መሆኑን እያወቀ በሳቢ ርዕስ አንባቢን ማወናበድ የለበትም። ርዕሱና መጽሐፉ ‹ማች› ያደርጉ ዘንድ የቻለውን ያህል መጣርና መሞከር አለበት። ለሸፋኑ ርዕስ እንደተጨነቀው ሁሉ ለይዘቱም መጨነቅ አለበት። ይህ ኢስላማዊ ሥነምግባር ነው።

አንድ ሙስሊም ታማኝነቱን ከሚገልፅባቸው መንገዶች መካከልም የሚጠቀስ ነው። ታማኝነት ለፈጣሪ መታመን፣ ከራስ ጋርም ሆነ ከሌሎች የሰው ልጆች ጋር እውነተኛ መሆን ነው። ከዚህም ባለፈ የዚህ ዓይነቱ ልፋትና ትኩረት ለሌሎችም አስተማሪ ይሆናል። መስሊሞች በሥነምግባራቸውና በሥራቸው ጥራት ከሌሎች ዓለማዊ ሰዎች

ለየት ብለው መገኘት አለባቸው። ሰዎች አንድን መጥፎ ነገር ስላደረጉ ማድረግ፣ መጥፎ ባህል ስለለመዱ መልመድ፣ ሌሎች ስላታለሉ ማታለል፣ ስላጭበረበሩ ማጭበርበር የለበትም። ሰው ስላጠፋ ማጥፋት፣ ሰው ሁሉ ስለከፋ መከፋት ትልቅ ጥፋት ነው። ይህን ያልኩት ራሴንና እናንተንም ለማስታወስ ያህል ነው።

እርግጥ ነው መጽሐፍ ከመፃፉም በላይ ርዕስ ማውጣቱ ለብዙዎች ይከብዳል። ለዚህም ነው ለምሳሌ የዚህን መጽሐፍ ርዕስ አራት ጊዜ ቀያይሬያለሁ። መጀመርያ "ከሰው ጋር ስለመኖር" አልኩት፣ ቀጥሎ "ሕይወት አስተማረችኝ" ብዬ ሰየምኩት፤ "የደስታ ሚስጥሮች"፣ እንዲሁም "የመኖር ጥበብ"... ብየውም ነበር።

በመጨረሻም ይሻላል ብዬ በማሰብ "ከአላህ ጋር" የሚል ርዕስ ሠጠሁት።

መጽሐፉ በአጠቃላይ ሀሳቡ ከአላህ ጋር የመሆንን አስፈላጊነት ያወሳል። ከአላህ ጋር ሲሆኑ የተመኙት ሁሉ እንደሚሳካ፣ ምድራዊ ደስታም ሆነ አኺራዊ ስኬት እንደሚገኝ ይገልፃል። እርግጥ ነው ሁሉም ነገር የተሟላ የሚሆነው ከአላህ ጋር ሲሆኑ ነው። ይህን የሚጠራጠር ሙስሊም ይኖራል ብዬ አላስብም። ከአላህ ጋር መሆን ሲባል ሁሌ እሱን በማሰብ በሃሳብ ሊሆን ይችላል፣ እሱን በማውሳትና በማወደስ ሊሆን ይችላል፣ እሱን በሁሉም ነገር ውስጥ በማስገባት ሊሆን ይችላል፣ በቃልም ሆነ በተግባር አላህን በማስታወስ ሊሆን ይችላል፣ በአምልኮ ተግባራት በመበርታት ሊሆን ይችላል... ሌላም ሌላ።

መጽሐፉ ከአላህ ጋር የተኖሩ የሕይወት ተሞክሮዎችን በማነሳሳት ከአላህ ጋር መኖር ለሕይወታችን ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ የሚያስታውስ ነው።

በርግጥ ብዙ ነገር አላውቅም። ጥቂት ነገሮችን ግን ሳላውቅ አልቀርም ብዬ አሰብኩ። ትምህርት ባያሳውቀኝ የሕይወት ልምድ በራሱ አስተምሮኛል። እነዚያን ነገሮች ለወንድም እህቶቼ ለማካፈል ወደድኩ። ተካፈሉኝ፤ አብረን እናንብብ።

ይህ "ከአላህ ጋር" የተሠኘው መጽሐፍ በሁሉ ነገር ውስጥ ከአላህ ጋር ስለመሆን ፋይዳን ለኔም ለናንተም ይሰብካል፤ ያመላክታል፣ ይጠቁማል። አስተዋሽ ሲጠፋ፣ ሃሳብ ሲገባን፣ ሲደብረን፣ ስልችት ሲለን፣ ሲጨንቀን፣ ስንባከን... ካስቀመጥንበት እናንሳው።

ከርዕሶቹ መካከል መርጠን በትኩረትና በመጋገም እናንብበው፤ በጥልቀትም እንየው። ኢንሻአላህ ተጠቃሚዎች እንሆናለን።

መልካም ንባብ።

ይህ መጽሐፍ ከእናቴ በኋላ እንደ እናቴ ለማያቸው ታላም ዘዋኩ ይሁንልኝ ። ጎንደር ቀበሌ 18 መስጊድ ።